የኢትዮጵያ
ደረጃ

desa
lege

Digitally signed by desalege
DN: cn=desalege, o=ESA, ou=standard development, email=desalegne46@gmail.com, c=ET
Date: 2020.10.12 11:56:30 +03'00'

ኢደ 6665:2021

የመጀመሪያ ዕትም

xx-xx-2021

# የስጋ ቤቶች የመጠጥ ደህንነት ፤አገልግሎት መስጫ ተቋማት ንፅህና እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

ICS:xx .ÈÈ.

Published by Ethiopian Standards Agency

©ESA

## **መቅድም** (foreword)

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ ንፅህና እና የጤና ነክ ተቋማትአገልግሎት ቴክኒክ ኮሚቴ (ቴኮ 205) ላይ መሰረት አድርጎ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ አማካኝነት እንደ አዲስ የታተመ ነው፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ ኢ.ደ 6665፡2021፤ የስጋ ቤቶች የመጠጥ ደህንነት ፤አገልግሎት መስጫ ተቋማት ንፅህና እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት ሲሆን በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ አማካኝነት እንደ አዲስ የታተመ ነው፡፡

የደረጃ መነሻ ሰነዱን ያቀረበው የጤና ሚኒስቴር ነው፡፡ኤጀንሲያችን ለሰነዱ አቅራቢ ምስጋናውን ያቀርባል ፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

# 1. ወሰን

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ በሁሉም ስጋ ቤቶች  የምግብ ደህንነት ፤አገልግሎት  መስጫ ተቋማት ላይ የንፅህና እና አካባቢ ጤና አጠባበቅን ያካተተ መስፈርት ነው፡፡

# 2. ማጣቀሻ

# 3. ቃላትና ትርጓሜ

## 3.1. ስጋ ቤት

የቀንድ ከብት፣ የበግ፣ የፍየል፣ የግመል እና የአሣማ ሥጋ በጥሬው የሚሸጥበት ድርጅት ማለት ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ መስፈርቶችን በማሟላት የበሰለና የጥሬ ስጋ አገልግሎትን የሚሰጥ ተቋም ማለት ነው፡፡

## 3.2.

**የስራ ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሶች**

የስራ ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሶች በስራ ቦታ ለሚከሰቱ ማንኛውም በንክኪ የጤና ችግር ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች ለመከላከል ሲባል የሚለበሱ/የሚደረጉ ቁሳቁሶች ናቸው፡፡

## 3.3.

**የተሟላ እጅ መታጠቢያ**

ሙቅና ቀዝቃዛ የቧንቧ ውሃ፣ ፍሳሽ መቀበያ ከሴራሚክ (በብሎኬት/ግንብ) የተሰራ ግንዱ፣ ፈሳሽ ሳሙና፣ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ማጽጃና የዕጅ ማድረቂያ ሶፍትና የፍሳሽ መስመር የተዘረጋለት ማለት ነው፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

3.4.

**የውሃ አቅርቦት**

ከከተማው የውሃ መስመር ወይንም አግባብ ባለው አካል ተመርምሮ ለሰው ልጅ ጥቅም እንዲውል የተረጋገጠ የጉድጓድ ወይም ከሌሎች የውሃ መገኛ ምንጮች የተገኘ ውሃ ማለት ነው፡፡

3.5.

**የመፀዳጃ ቤት**

ሰዎች በቁም ወይም በመቀመጥ ከሰውነት የሚወጣ ቆሻሻ (አይነምድር እና ሽንት) የሚያስወግዱበት መቀመጫ፣ በር፣ ወለል፣ ግድግዳ እና ጣሪያ/ኮርኒስ ያለው ክፍል ነው፡፡

3.6.

**በቂ ብርሃን**

ማንኛውም ማየት የሚችል ተጠቃሚ የሚገለገልበትን ክፍል አራቱንም ጥጎች ያለምንም ችግር ማየት የሚችልበት አካባቢ ማለት ነዉ፡፡

3.9.

**ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ**

ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ፣ በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፣ ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ፤ በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ ለማጽዳት ቅርፁ አመቺ የሆነ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችል የቆሻሻ መሰብሰቢያ ማለት ነው፡፡

# 4. መስፈርቶች

## 4.1. አጠቃላይ መስፈርቶች

4.1.1. የስጋ ቤት የተሟሌ የመጠጥ እና የስጋ ምርቶች አቀባበልና አያያዝ የአሰራር መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡



©ESA

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

4.1.2. ድርጅቱ በሌላ የንግድ ዘርፍ ያልተያዘ ወይም በተደራቢ ሌላ ንግድ የማይካሄድበት ከመኖሪያ ቤትም ጋር በግድግዳ ያልተያያዘና እራሱን የቻለ መሆን አለበት፡፡

4.1.3. የመሰረተ ልማት አውታሮች ማለትም መብራት፣ ውሀ፣ ስልክና መንገድ የተሟሉለት መሆን አለበት፡፡

4.1.4. በክፍሉ የተሟላ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን እና በቅርብ የተሞላ እና የታደሰ እሳት አደጋ ማጥፊያ መኖር አለበት፡፡

4.1.5. የሥጋ ማጓጓዣ የሆኑ ዕቃዎች ጥራት ያላቸውና ንጽህናቸው የተጠበቀ መሆን አለበት፣ በንጽህና ለመጠበቅም አመቺ ሆነው የተሠሩ መሆን አለባቸው፡፡

4.1.6. ድርጅቱ ከማዘጋጃ ቤት የቧንቧ ውሃ ወይም አግባብ ባለው አካል ተመርምሮ ለሰው ልጅ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደ የጉድጓድ ወይም የውሃ መገኛ ምንጮች የተገኘ ውሃ መኖር አለበት፡፡

4.1.7. የድርጅቱ ሰራተኞች በሚሰሩበት መደብ በሙያው የሰለጠኑ መሆን አለባቸው፡፡

4.1.8. ማንኛውም ሰራተኛ ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ገላውን መታጠብ አለበት፣ ንፅህናውን የጠበቀ የስራ ልብስ በስራ ላይ ለብሶ መገኘት አለበት፡፡

4.1.9. የኤሌክትሪክ ገመዶች በማይታይና ሰራተኞች ላይ አደጋ በማያስከትል መልኩ የተዘረጋ መሆን አለበት፡፡

4.2. ድርጅቱ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጊዜያት በሙሉ መፀዳጃ ቤቱ ለተገልጋይ ክፍት መሆን አለበት፡፡

4.2.1. ከምግብ ጋር ንክኪ ያለው ሰራተኛ የእጅ ጥፍርን በየጊዜው በአጭሩ መቆረጥ አለበት ተንጠልጣይ የጆሮ ጌጥ፣ የእጅ ቀለበት፣ ሰአት እና የእጅ አንባር በስራ ቦታ ማድረግ የለበትም፡፡ ፀጉር ሙሉ በሙሉ ሊሸፍኑ በሚችሉ የስራ ኮፍያዎች መሸፈን አለበት፡፡

## 4.3. ዝርዝር መስፈርቶች

### 4.3.1. የአካባቢያዊ ሁኔታ

4.3.1.1. ከኢንዱስትሪዎችና ከቆሻሻ መጣያ አካባቢዎች ቢያንስ 100 ሜትር የራቀ መሆን አለበት፡፡

### 4.3.2. የህንፃው የዲዛይንና የግንባታ ሁኔታ

4.3.2.1. የአካል ውስንነት ላለባቸው የጋሪ መንቀሳቀሻ ምቹ የሆነ መወጣጫ (ራምፕ) ቢበዛ 15 ዲግሪ ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4.3.2.2. መስኮትና በሮች ተባይ፣ ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳት የማያስገቡ መሆን አለባቸው፡፡

### 4.3.3. የአገልገሎት ተጠቃሚዎች ማስተናገጃ ክፍል

4.3.3.1. ክፍሉ ቢያንስ 3 ሜትር በ4ሜትር ከ12 እስከ 16 ተጠቃሚ/ሰው የሚያስተናግድ ሆኖ  ስፋቱ በዚሁ መጠን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡

©ESA

**4.3.4. ስጋ ቤት**

4.3.4.1. የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 3ሜትር በ 3ሜትር መሆን አለበት፡፡

4.3.4.2. ክፍሉ በድርጅቱ ግቢ ከደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ፣ ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን/ሴፕቲክ ታንክ/ ፣ከጽዳትና ሌሎች ኬሚካሎች ማስቀመጫ መጋዘን ቢያንስ 10 ሜትርና ከዛ በላይ የራቀ መሆን አለበት፡፡

**4.3.5. የሥጋ ማስቀመጫ ቦታ**

4.3.5.1. የቅዝቃዜ መጠኑ ከ-18 እስከ -22 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ መሆን አለበት፡፡

4.3.5.2. ዝንብ፣ በረሮ አይጥና ከሌሎች ነፍሳቶች የማይገኙበት መሆን አለበት ፡፡

4.3.5.3. ለእይታ በግልፅ የሚታይ ቦታ ላይ የተቀመጠ ፍሪጅ መኖር አለበት፡፡

**4.3.6. የስጋ መጥበሻ ክፍል ደረጃ (አገልግሎቱን የሚሰጥ ከሆነ)**

4.3.6.1. የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 9 ካ.ሜ /3ሜትር በ3ሜትር/ መሆን አለበት፡፡

4.3.6.2. የዕንጨት ማገዶ ማብሰያ ምድጃ በድርጅቱ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ ክፍሉ የጭስ ማውጫ ከጣሪያ በላይ 2 ሜትር ከፍታ ያለው መኖር አለበት፡፡

4.3.6.3. ክፍሉ በድርጅቱ ግቢ ከደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ፣ ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን/ሴፕቲክ ታንክ/ ፣ከጽዳትና ሌሎች ኬሚካሎች ማስቀመጫ መጋዘን ቢያንስ 10 ሜትርና ከዛ በላይ የራቀ መሆን አለበት፡፡

**4.3.7. የእቃ ማጠቢያ ሲንክ**

4.3.7.1. ለዕቃዎች ማጠቢያ ባለሶስት ጉድጓድ ሲንክ ከፍሳሽ ማስወጋጃ ቱቦ ጋር የተያያዘ መዘጋጀት አለበት፡፡

4.3.8. **የውሃ አቅርቦት**

4.3.8.1. በድርጅቱ የሚዘረጉ የውሃ ማከፋፈያ መስመሮች ሙሉ በሙሉ የመሰበር/መሰንጠቅ ችግር የሌለባቸውና የማያፈሱ ወይም ስርገት የሌላቸው መሆን አለባቸው፡፡

4.3.8.2. የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚ ከፕላስቲክ ወይም ከፋይበር ግላስ (fiber glass) የተመረተ መሆን አለበት፡፡

4.3.8.3. የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚያው ውሃ በሚቋረጥበት ወቅት የመያዝ አቅሙ ቢያንስ ለሁለት ቀን ማገልገል የሚችል መሆን አለበት፡፡

**4.3.9. የመፀዳጃ ቤት ሁኔታ**

4.3.9.1. የመፀዳጃ ቤት ክፍል ጣሪያ ከፍታ ቢያንስ 2.4 ሜትር (ሁለት ነጥብ አራት ሜትር) መሆን አለባቸዉ፡፡

4.3.9.2. የክፍሉ ስፋት 1.2 ሜትር በ1.2 ሜትር መሆን አለበት፡፡

4.3.9.3. ለ20 (ሃያ) ወንበር ወይም ተገልጋይ አንድ የመፀዳጃ መቀመጫ ለወንድ እና ለሴት የተለየ መሆን አለበት፡፡

4.3.9.4. አንድ የሽንት መሽኒያ (ዩሪናል) ለ20 (ሃያ) ወንበር ወይም ተገልጋይ ሊኖር ይገባል፡፡

4.3.9.5. ከመፀዳጃ ቤቱ ቢበዛ በሶስት ሜትር ርቀት አገልግሎት የሚሰጥ አግባብነት ያለው (በግድግዳ ላይ የተገጠመ ሲንክ/ገንዳ ከወራጅ ውሃ ጋር ያለው) የእጅ መታጠቢያ መኖር አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD



©ESA

4.3.10. **የሰራተኛ ገላ መታጠቢያ**

4.3.10.1. የገላ መታጠቢያ ክፍል ጣሪያ 2.4 ሜትር (ሁለት ነጥብ አራት ሜትር) ከፍታ ያለዉ መሆን አለበት፡፡

4.3.10.2. የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 1.2 ሜትር*1.2 ሜትር (አንድ ነጥብ ሁለት ሜትር በአንድ ነጥብ ሁለት ሜትር) መሆን አለበት፡፡

4.3.10.3. የመታጠቢያ ክፍሉ ንጹህ አየር ማስገቢ ከኮረኒስ 20 ሳ.ሜ ዝቅ ብሎ በ45 ዲግሪ ወደታች ተከፋች የሆነ መስኮት መኖር አለበት፡፡

4.3.10.4. ለ20 ሰራተኛ በንፅፅር አንድ የወንድ አንድ የሴት ሻወር ሊኖር ይገባል፡፡

4.3.11. **የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ**

4.3.11.1. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ከምንጬ (በስራ እንቅስቃሴ ከሚመነጭበት ቦታ) መሰብሰብ አለበት፡፡

4.3.11.2. የቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ማቆያ (garbage bin) ሶስት አራተኛው ሲሞላ ወደ ድርጅቱ አጠቃላይ መሰብሰቢያ መገልበጥ አለበት፡፡

4.3.12. **የድርጅቱ ሰራተኞች**

4.3.12.1. ድርጅቱ በስሩ የሚሰሩ ሰራተኞች በዚህ ደረጃ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች እና የአሰራር ቅደም ተከተሎች ላይ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ መሰልጠናቸውን ማረጋገጥ አለበት ፡፡

4.3.12.2. ማንኛውም ሰራተኛ ከምግብ ወለድ በሽታ ነጻ መሆን ስላለበት በአመት አራት ጊዜ/በየሶስት ወሩ/ የጤና ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4.3.12.3. ለሰራተኞችነጭ/ፈካ ያለ ሙሉ የስራ ልብስ ባለቅያሬ መኖር አለበት፡፡

## 5. የድርጅቱ አሰራር ዘይቤ

5.1.1. የስጋ ቤት የተፃፈ የዕቃ አስተጣጠብ (Cleaning, sanitizing and dish washing) የአሰራር መመሪያ መኖር አለበት፡፡

5.1.2. የስጋ ቤት የተፃፈ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር መመሪ መኖር አለበት፡፡

5.1.3. የስጋ ቤት የተፃፈ የእጅ አስተጣጠብ እና የግል ንፅህና የአሰራር መመሪያ መኖር አለበት፡፡

5.1.4. የስጋ ቤት የተፃፈ የተበላሹ መጠጦችና ዕቃዎች አወጋገድ የአሰራር መመሪያ መኖር አለበት፡፡

5.1.5. አካባቢዉ ረግረግማነት የሌለዉና ናዳ የማያሰጋዉ መሆን አለበት፡፡

5.1.6. የስጋ ቤት የሚከተሉት አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ማለትም፡-

- መመገቢያ ክፍል
- የዕቃ ማስቀመጫ መጋዘን

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

- የሰራተኛ ልብስ መቀየሪያ ክፍል
- እጅ መታጠቢያ
- መፀዳጃ እና ገላ መታጠቢያ ክፍሎች መኖር አለባቸው፡፡

5.1.7. የድርጅቱ ሕንፃ ያረፈበት ወይም የሚያርፍበት ቦታ፣አፈሩ የዝናብም ሆነ ጎርፍ ዉሃን በቀላሉ ሊያቁር የማይችል መሆን አለበት፡፡

5.1.8. በአካባቢውና በቅጥር ግቢ ውስጥ ለቆርጣሚ እንስሳና ለነፍሳት መራቢያነት አመቺ ሁኔታ መኖር የለበትም፡፡

## 6. የህንፃው የዲዛይንና የግንባታ ሁኔታ

6.1. ህንፃው የተገነባበት ግብአት ከድንጋይ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላ ወይም ከተመሳሳይ ግብአት የተገነባ እና በሲሚንቶ ሊሾ የተለሰነና ልሙጥ መሆን አለበት፡፡

6.2. ህንጻው የተገነባበት ግብአት የእሳት አደጋን መቋቋም የሚችል መሆን አለበት፡፡

6.3. የክፍሉ ስፋት ድርጅቱ በሚሰጠው አገልግሎት ላይየመበከል፣ የመመረዝ እና የመደበላለቅ ሁኔታ የማያመጣ ሆኖ ስራውን በትክክል ሊያሰራ በሚያስችል መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፡፡

6.4. የድርጅቱ ህንፃውም ሆነ በውስጡ ያሉት ክፍሎች የመሠረቱ አሠራር ውሃን፣ ተባይ፣ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳትን የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

6.5. የድርጅቱ ህንጻ ያረፈበት ቦታ አፈር ዝናብም ሆነ ጎርፍ በቀላሉ የማያቁር መሆን አለበት፡፡

6.6. መስኮቶችና በሮች በቀላሉ መከፈትና መዘጋት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

6.7. ወለሉ ለማፅዳት የሚያመች ያልተሰነጣጠቀና ደረጃውን ከጠበቀ የግንባታ ቁሳቁሶች የተሰራ (ሲሚንቶ፣ ኮንክሪት፣ ሴራሚክ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ የግንባታ ቁሳቁስ)፣የማያዳልጥና በቀላሉ ሊታጠብ የሚችልና የውሃ ፍሳሽ ወደ አንድ አቅጣጫ በተዳፋት ሊፈስ በሚችል መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፡፡

6.8. ግድግዳው ለማፅዳት የሚያመች ፈካ ያለ ወይም ነጭ ታጣቢ ቀለም የተቀባ ያልተሰነጣጠቀና ደረጃውን ከጠበቀ የግንባታ ቁሳቁሶች የተሰራ መሆን አለበት (ሲሚንቶ፣ ኮንክሪት፣ ሴራሚክ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ የግንባታ ቁሳቁስ)፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

 ©ESA

6.9. ኮርኒስ ለማፅዳት የሚያመች፣ ፈካ ያለ/ነጭ ቀለም የተቀባ ያልተከፈተ/ያልተቀደደ፣ ሙቀትን መቋቋም ከሚችል ደረጃውን ከጠበቀ የግንባታ ቁሳቁሶች የተሰራ መሆን አለበት (ከስላብ፣ ማይካ/ኢፖክሲ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ የግንባታ ቁሳቁስ) ፡፡

## 7. የአገልገሎት ተጠቃሚዎች ማስተናገጃ ክፍል

7.1. የክፍሉ ሁኔታ፡-ወለል፣ ግድግዳና ኮርኒስ በአንቀጽ በ6.3፣6.7፣6.8፣እና 6.9 የተገለፀውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

7.2. ያልተሰነጣጠቀ፣ ከቆሻሻ የፀዳ፣ የቧንቧና ፍሳሽ መስመሮች እንጥብጣቢና ፍሳሽ የሌለው፤ ሊፀዳና ሊታጠብ በሚችል ሁኔታ ፈካ ያለ ቀለም የተቀባና በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ መሆን አለበት፡፡

7.3. ከማንኛውም ዓይነት ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ፣ ቆርጣሚ እንስሳትና ሌሎች ነፍሳት የፀዳ መሆን አለበት፡፡

## 8. የስጋ መሸጫ ክፍል

8.1. የስጋ ቤት የክፍሉ ሁኔታ፡-ወለል፣ ግድግዳና ኮርኒስ በአንቀጽ በ6.3፣6.7፣6.8፣እና 6.9 የተገለፀውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

8.2. ክፍሉ ክፍት መስኮት ሊኖረው አይገባም፤ ደንበኞች የሚሸጠውን ስጋ እንዲያዩ ከተፈለገ በመስታወት የተሰራ መከለያ ሊኖረው ይገባል፡፡

8.3. ንጽህናቸው የተጠበቀና የማይዝጉ ሜንጦዎች መኖር አለባቸው፡፡

8.4. አገልግሎት የሚሰጥ የዝንብና የትንኝ መያዣ (መግደያ) (Fly Trap) መኖር አለበት፡፡

## 9. የሥጋ ማስቀመጫ ቦታ

9.1. የተቆራረጠ ሥጋ የቅዝቃዜ መጠኑ ተጠብቆ ከላይ በተገለፀው አቀማመጥ መሰረት መቀመጥ አለበት፡፡

9.2. ንጽህናቸው የተጠበቀና የማይዝጉ ሜንጦዎች መኖር አለባቸው፡፡

9.3. አገልግሎት የሚሰጥ የዝንብና የትንኝ መያዣ (መግደያ) (Fly Trap) መኖር አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

## 10. የሥጋ መቆራረጫ ጠረጴዛ

10.1. በልስላሴ የተላገ ወይም ከእምነበረድ የተሠራና በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡

10.2. የቢላዋና ሞረድ ማስቀመጫ መሣቢያ ከጠረጴዛው ጋር መሠራት አለበት፣መሳቢያው አገልግሎት መስጠት የሚኖርበት ቢላዋና ሞረድን ለማስቀመጥ ብቻ ሲሆን ሌሎች ቁሳቁሶች በመሳቢያው መቀመጥ አይኖርባቸውም፡፡

## 11. የስጋ መጥበሻ ክፍል (አገልግሎቱን የሚሰጥ ከሆነ)

11.1. ወለል፣ግድግዳውና ኮርኒስ በአንቀጽ በ6.3፣6.7፣6.8፣እና 6.9 የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት አለባቸዉ፡፡

11.2. ከማብሰያዉ የሚወጣዉን እንፋሎትና ሙቀት/የታመቀ አየር/ማስወገጃ ዘዴ (ሳከር) መኖር አለበት፡፡

11.3. ከደረቅና ከፍሳሽ ቆሻሻ የፀዳ እና ምንም አይነት ቆርጣሚ እንስሳትና ነፍሳት የማይታይበት መሆን አለበት፡፡

11.4. በቂ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የአየር ዝውውርና የብርሃን መጠን መኖር አለበት፡፡

11.5. በክፍሉ ውስጥ ለሰራተኞች የተሟላ እጅ መታጠቢያ መኖር አለበት፡፡

11.6. ደረቅ ቆሻሻን ጊዜያዊ መሰብሰቢያ/ማቆያ ክዳን ያለውና በእግር የሚከፈትና የሚዘጋ፣ በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፣ ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁስ የተሰራ፤ በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ ለማጽዳት ቅርጹ አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችል ማጠራቀሚያ መዘጋጀት አለበት፡፡

11.7. አገልግሎት የሚሰጥ የዝንብና የትንኝ መያዣ (መግደያ) (Fly Trap) መኖር አለበት፡፡

11.8. የማብሰያ እቃዎች ያልተሰነጣጠቁ፣ ያልተሰባበሩ፣ የልተሸራረፉ፣ ያላረጁ፣ ከማይዝግ ቁስ የተሰሩ መሆን አለባቸው፡

11.9. መጸዳጃ ቤቱ ከስጋ ቤቱ 10 ሜትር መራቅ አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

## 12. የመገልገያ ዕቃዎች ዝግጅትና የንጽህና የአያያዝ

12.1. እያንዳንዱ ስጋ ቤት ትልቁ ማቀዝቀዣ ወይም ዲፕ ሪፍሪጀሬተር ሊኖረዉ ይገባል፡፡

12.2. የሥጋ መፍጫ፣ የአጥንት መቁረጫ ማሽን ካላቸው ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኃላ መጸዳት አለበት፡፡

12.3. ለሥጋ መጠቅለያ የሚሆን ሌጣ የሆነ ወረቀት መኖር አለበት፡፡

12.4. የእጅ መታጠቢያ ሲንክ ከማይቆራረጥ የቧንቧ ውሃና ፍሳሽ ከተፈቀደ የፍሳሽ መስመር ወይም ከፍሳሽ ማጠራቀሚ ጋር ተያይዞ የሚወገድ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የእጅ ማጽጃ ሣሙና መኖር አለበት፡፡

12.5. ለዕቃ ማጠቢያ ሙቅ ውሃ ያለው ሲንክ መኖር አለበት፡፡

## 13. የእቃ ማጠቢያ ሲንክ

13.1. የማጠቢያ ውሃ ሙቅና ቀዝቃዛ በቧንቧ መስመር የሚመጣ መዘጋጀት አለበት፡፡

13.2. ለዕጥበት የሚያገለግሉ ሳሙናዎችና ኬሚካሎች በበቂ መጠን በአቅራቢያ መሟላት አለበት፡፡

13.3. የታጠቡ እቃዎች እንዲደርቁ ማንጠፍጠፊያ ከፕላስቲክ (የማይበሰብስና ዝገትን መቋቋም የሚችል) ቁሳቁስ የተሰራ ራክ መኖር አለበት፡፡

13.4. የማጠቢያ ሲንኩ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦ የተገጠመለት ሆኖ ቱቦው ከተፈቀደ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ወይም ከፍሳሽ ማጠራቀሚያ ጋን/ሴፕቲክ ታንክ/ ጋር የተገናኘ መሆን አለበት፡፡

13.5. የፍሳሽ መስመሩ ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን መስሪያ ቤት የፍሳሻ መስመር ጋር የተገናኘ ከሆነ የሁለቱን ስምምነት የሚገልጽ የውል ስምምነት መቅረብ አለበት፡፡

14. እጅን ቀጥሎ ከቀረቡት ተግባራትና ሁኔታዎች በየጊዜው በሳሙና መታጠብ ያስፈልጋል፡ -

- ከመጸዳጃ ቤት መልስ፤
- በስራ መሃል ዕረፍት ከተሰወሰደ በኋላ፤
- ማንኛውንም የሰውነትን አካል በስራ መሃል ከተነካ በኋላ፤
- ከምግብ በፊትና በኋላ፤

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

- ቆሻሻ ወይም ማንኛውም የማጽጃ ቁስና ኬሚካሎች ከተነካ በኋላ፤
- ማንኛውንም የጽዳት ስራ ከማከናወን በኋላ፤
- ጓንት ከመጠቀም በፊትና በኋላ፤
- የእጅ ጥፍርን በየጊዜው በአጭሩ መቆረጥ ያስፈልጋል፤
- የምግብ ዝግጅት ላይየ ተሰማሩ ሰራተኞች፡ ተንጠልጣይ የጆሮ ጌጥ፣ የእጅ ቀለበት፣ ሰአት እና የእጅ አንባር በስራ ቦታ መደረግ የለበትም፤
- ፀጉር ሙሉ በሙሉ ሊሸፍኑ በሚችሉ የስራ ኮፍያዎች መሸፈን አለበት፡፡

## 15. ተጨማሪ አገልግሎቶች

### 15.1. የአየርዝውውርእናየብርሃን

15.1.1. በድርጅቱ ክፍሎች በቂ የአየር ዝውውር መኖር አለበት፡፡

15.1.2. አገልግሎት ለመስጠት በቂ የሆነ ብርሃን መኖር አለበት ፡፡

15.1.3. አማራጭ የሃይል ምንጭ (generator) ሊኖር ይገባል፡፡

## 16. የመፀዳጃ ቤት ሁኔታ

16.1. የክፍሉ ወለል እና ግድግዳ መታጠብ፣ መፅዳት የሚችል፣ በውሃ የማይቦረቦር እና ልስላሴ ካለው የግንባታ ቁሳቁስ መሰራት አለበት፡፡

16.2. መፀዳጃ ቤቱ በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በ10 ሜትር ርቀት የተሰራ መሆን አለበት፡፡

16.3. ክፍሉ ንፅህናው የተጠበቀ መሆን አለበት ፡፡

16.4. ከመጥፎ ሽታ ነፃ መሆን አለበት ፡፡

16.5. የክፍሉ በር በቀላሉ ከውስጥ በኩል መከፈትና መዘጋት የሚችል መሆን አለበት፡፡

16.6. በመጸዳጃ ቤቱ ዉስጥ በውሃ ግፊት የሚሰራ ፍሳሽ እና ጽዳጅ ማስረጊያ መኖር አለበት፡፡

16.7. ክፍሉ በቂ የሆነ ብርሃን ማግኘት አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD



©ESA

19.3. ቁሳቁስ የተሰራ) ወይም ከተፈቀደ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት አለበት፡፡

19.4. ድርጅቱ የፍሳሽ ቆሻሻን ለመሰብሰብ የሚጠቀመው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን (ሴፕቲክ ታንክ) ከሆነ ሊሞላ 50 ሳንቲ ሜትር ሲቀረው መመጠጥ አለበት፡፡

19.5. ማንኛውም የፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ዝናብ ውሃ ማስወገጃ መስመር ወይም ወደ አካባቢ መለቀቅ የለበትም፡፡

19.6. የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ የሚመለከተው አካል ከተፈቀደ የፍሳሽ መስመር ጋር የተያያዘበት፣የተጠራቀመ ፍሳሽ የተመጠጠበት ሲጠይቅ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## 20. ሲጋራ የማስጨስ ደንብ

20.1 ድርጅቱ ሲጋራ ማጨስ የሚከለከልበትን አዋጅ መተግበር አለበት፡፡

## 21. የድምፅብክለት

21.1. ከድርጅቱ /እንደ ተቋሙ ባህሪ/ የሚወጣው ድምጽ አካባቢን እንዳይበክል በህግ ከተፈቀደው የድምጽ ልኬት መጠን በታች መሆን አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

16.8. መጸዳጃ ቤት ውሰጥ ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ፣በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፣ለማጽዳት ቅርፃቸው አመቺ የሆኑ፣ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት ከማይችሉ ቁሶች የተሰራ ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መኖር አለበት፡፡

16.9. ለእጅ መታጠቢያ የሚሆን ደረቅ ወይም ፈሳሽ ሳሙና መኖር አለበት፡፡

16.10. ድርጅቱ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጊዜያት በሙሉ መፀዳጃ ቤቱ ለተገልጋይ ክፍት መሆን አለበት፡፡

## 17. የሰራተኛ ገላ መታጠቢያ

17.1. የክፍሉ ወለል ወለል እና ግድግዳ መታጠብ፣ መፅዳት የሚችል፣ በውሃ የማይቦረቦር እና ልስላሴ ካለው የግንባታ ቁሳቁስ መሰራትአለበት፡፡

17.2. የክፍሉ ወለል በጽዳትና በአገልግሎት ጊዜ ምንም አይነት ፍሳሾችን አቁሮ መያዝ የለበትም፡፡

17.3. ሻወር ቤቱ ከመፀዳጃ ክፍል የተለየ እና ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

17.4. የክፍሉ በር በቀላሉ ከውስጥ በኩል መከፈትና መዘጋት የሚችል መሆን አለበት፡፡

17.5. ለመታጠቢያ ቦታ አደጋን የሚከላከል (ከፕላስቲክ የተሰራ) መረጋገጫ መዘጋጀት አለበት፡፡

17.6. ሻወር ለወንድና ለሴት በሚል ንፅፅር የተለየ መሆን አለበት፡፡

17.7. በቂ የሆነ የአየር ዝውውር ሊኖረው ይገባል፡፡

17.8. የፍሳሽ መስመሩ ከተፈቀደለት የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር ወይም ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን (ሴፕቲክ ታንከር፡ ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ የተሰራ፣ ሙሉ በሙሉ የተሸፈነ/ድፍን የሆነና ወደ ውጭም ሆነ ወደ ውስጥ ፍሳሽ በማያሰርግ የግንባታ ቁሳቁስ የተሰራ) ጋር የተገናኘ መሆን አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD


©ESA

## 18. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ

18.1. ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመሰብሰቢያ ክዳን ያለውና በእግር ተረግጦ የሚከፈትና የሚዘጋ ጊዜያዊ እና በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማጠራቀሚያ/ማቆያ መኖር አለበት (ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት ቅርፃቸው አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችሉ)

18.2. የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የሚቀመጡበት ቦታ አካባቢ ንጽህናው የተጠበቀ ከተባይ፣ከነፍሳት እና ከቆርጣሚ እንስሳት ነፃ መሆን አለበት፡፡

18.3. በተቋሙ የተለያዩ ቦታዎች የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች/መሰብሰቢያዎች መቀመጥ አለባቸው፡፡

18.4. ድርጅቱ የደረቅ ቆሻሻን በአይነት እና በባህሪያቸው (የሚበሰብሱ እና የማይበሰብሱ) በመለየት መሰብሰብና ማስወገድ አለበት፡፡

18.5. ድርጅቱ የመጨረሻ/አጠቃላይ የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ቦታ ላይ ከድርጅቱ ለሚመነጨው የደረቅ ቆሻሻ ተመጣጣኝ የሆነ ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መኖር አለበት (ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት ቅርፁ አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችል እና እንደ ቆሻሻው አይነት የተለየ)

18.6. መጨረሻ የተሰበሰበው ቆሻሻ በተገቢው  መንገድ መወገድ አለበት፡፡

## 19. የፍሳሽ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አወጋገድ

19.1. ድርጅቱ በአግባቡ የተሰራ በፕላን የተዘረጋ ፤ ከእይታ የተሸፈነ፣ ወደ ውጪ ፍሳሽ የሌለው የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

19.2. ድርጅቱ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች  (ከዕቃ ማጠቢያና ከዕጅ መታጠቢያ ሲንክ፣ ከመታጠቢያ ክፍሎች፣ ከመጸዳጃ ቤትየሚመነጭ  ማንኛውም ፍሳሽ ቆሻሻ ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ በተሰራ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን (ሴፕቲክ ታንክ፡ ሙሉ በሙሉ የተሸፈነወደ ውጭም ሆነ ወደ ውስጥ ፍሳሽ በማያሰርግ የግንባታ

DRAFT ETHIOPIA STANDARD

# እዝል ሀ

## የዕቃ አስተጣጠብ ቅድም ተከተል

ቅድመ ዕጥበት፡- የተራረፉ ምግቦችን ማራገፍ

ዕጥበት፡-በሞቀ ውሃ ሳሙናዎችን እና ኬሚካሎችን በመጠቀም ቅባት እና ቆሻሻን ማጠብ፤ አስፈላጊ ከሆነ በማጠቢያ ኬሚካሎች ከ2-3 ደቂቃ መዘፍዘፍ

ማለቅለቅ፡- የቀሩቆሻሻዎችንናአረፋዎችንበወራጅውሃማለቅለቅ

ማጽዳት፡- በሽታ አምጪ ተህዋሲያንን በሚገድል ኬሚካል ማጽዳት

የመጨረሻ ማለቅለቅ፡- በወራጅ ውሃ በሽታ አምጪ ተህዋሲያንን ገዳይ ኬሚካሉን ማጽዳት

ማድረቅ፡- በአየር እንዲደርቅ በማንጠፍጠፊያ /ራክ/ ላይ ወይም በማድረቂያ ማሽን በማድረግ ማድረቅ ፡፡

DRAFT ETHIOPIA STANDARD



©ESA

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ
Ethiopian Standards Agency

## *Organization and Objectives*

The Ethiopian Standards Agency (ESA) is the national standards body of Ethiopia established in 2010 based on regulation No. 193/2010.ESA is established due to the restructuring of Quality and Standards Authority of Ethiopia (QSAE) which was established in 1998.

***ESA's objectives are:-***

- Develop Ethiopian standards and establish a system that enable to check whether goods and services are in compliance with the required standards,
- Facilitate the country's technology transfer through the use of standards,
- Develop national standards for local products and services so as to make them competitive in the international market.

## Ethiopian Standards

The Ethiopian Standards are developed by national technical committees which are composed of different stakeholders consisting of educational Institutions, research institutes, government organizations, certification, inspection, and testing organizations, regulatory bodies, consumer association etc. The requirements and/ or recommendations contained in Ethiopian Standards are consensus based that reflects the interest of the TC representatives and also of comments received from the public and other sources. Ethiopian Standards are approved by the National Standardization Council and are kept under continuous review after publication and updated regularly to take account of latest scientific and technological changes. Orders for all Ethiopian Standards, International Standard and ASTM standards, including electronic versions, should be addressed to the Documentation and Publication Team at the Head office and Branch (Liaisons) offices. A catalogue of Ethiopian Standards is also available freely and can be accessed in from our website.

ESA has the copyright of all its publications. No part of these publications may be reproduced in any form without the prior permission in writing of ESA.

International Involvement

ESA, representing Ethiopia, is a member of the International Organization for Standardization (ISO), and Codex Alimentarius Commission (CODEX). It also maintains close working relations with the International Electro-technical Commission (IEC) and American Society for Testing and Materials (ASTM).It is a founding member of the African Regional Organization for standardization (ARSO).

***More Information?***
***Contact us at the following address.***
***The Head Office of ESA is at Addis Ababa.***

***☎ 011- 646 06 85, 011- 646 05 65***
***011-646 08 80***
***✉ 2310 Addis Ababa, Ethiopia***
***E-mail: info@ethiostandards.org,***
***Website: www.ethiostandards.org***

**Standard Mark**

DRAFT-ETHIOPIA STANDARD